# ደምብ - ሥርዓት

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

ተዛማጅ ግብአቶች፡- ABA, ABA-RB, BBB, CNA-RB, CND, CND-RA, COB-RA, GCA-RA
ኃላፊ ጽ/ቤት፡- Deputy Superintendent of School Support and Improvement
የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ

## በትምህርት ቤት ወይም በትምህርት ቤት ንብረት አካባቢ ሽያጭ-ችርቻሮ

I. **ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ ወይም በአካባቢው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ትምህርት ቤት ህንፃ ውስጥ በትምህርት ቀን የሚደረጉ ሽያጮችን ጨምሮ ላልተፈቀደ የሽያጭ እንቅስቃሴ ምላሽ የመስጠት አሠራር ለመዘርጋት

II. **ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች**

A. ሻጭ በማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል 500 ጫማ ቅርበት ላይ ህዝብ በሚተላለፍበት መንገድ ላይ ወይም በእግረኛ መንገድ ላይ በተለየ ፕሮግራም ምክንያት በርእሰመምህር ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውንም አይነት እቃ መሸጥ ወይም ለመሸጥ ማቅረብ አይፈቀድም። በ MCPS የማይመራ የካውንቲ ወይም የከተማ አስተዳደር-የማዘጋጃ ቤት የፈቃድ አሰጣጥ ደምቦችም ተግባራዊ ይደረጋሉ።

B. በትምህርት ቀን በ MCPS ትምህርት ቤት ህንፃ ለሚገኙ ሠራተኞች፣ ለተማሪዎች፣ ወይም ለሌሎች የትምህርት ቤት ማህበረሰቦች ሽያጭን-ቢዝነስን ለማስተዋወቅ የሚፈልግ-የምትፈልግ ሻጭ-ቬንደር ከርእሰመምህር/ከተወካዩ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበ(ባ)ታል።

C. ርእሰመምህራን በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ንብረት አካባቢ፣ ወይም አጠገብ የሽያጭ እንቅስቃሴ ሊፈቀድ ስለሚችልበት ሁኔታ ከትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻል ዲፖርትመንት-School Support and Improvement መመሪያ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ርእሰመምህራን እነዚህን ፋይዳ ያላቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድን ፖሊሲዎችና ደምቦች "Montgomery County Board of Education Policy BBB"፣ Ethics-ስነምግባር፣ እና "MCPS Regulations CNA-RB"፣ Advertising-ማስተዋወቅ፣ እና GCA-RA፣Conflict of Interest-ስለ ጥቅም ግጭት፤ ግንዛቤ መስጠት አለባቸው።

D. ከርእሰመምህር ፈቃድ ሳይሰጥ ማንኛውም ሰው በማንኛውም አይነት ሽያጭ ከተሰማራ(ች)፣ ህግ እየጣሰ(ች) ስለሆነ ቦታውን እንዲለቅ-እንድትለቅ በትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር(ት) አማካይነት ይገለጽላቸዋል።

E. ግለሰቡ(ቧ) በህግ የተከለከለውን አካባቢ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ካልሆነ(ች)፣ ርእሰመምህር/ተወካይ ለፖሊስ ያሳውቃል-ታሳውቃለች።

F. በ "MCPS Regulation COB-RA" ደምብ ላይ ከባድ ክስተቶችን ሪፖርት ስለማድረግ/Reporting a Serious Incident በተገለጸው መሠረት የክትትል ሪፖርት ፋይል ይደረጋል።

**ተዛማጅነት ያላቸው ምንጮች፦** Montgomery County Code, §47-2, Hours and places of operation; Code of Montgomery County Regulations, §47.02.01.05.2(a)(10), §47.02.01.05.2(b)(3), and §47.02.01.05.3(c)(6)

**ስለ ደንቡ ታሪክ፦** የበፊት ደንብ ቁ. 270-3, October 4, 1974; reviewed 1989; revised May 15, 1995; formerly Regulation COD-RA; revised October 14, 2008; revised April 16, 2018.